# የፈንድ አሰባሰብና አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት

# አሁን ያለው ሁኔታ መረዳት

# (Understanding the Current process /AS-IS/)

## መግቢያ

የአብክመ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክ/ጽ/ቤት የኤችአይቪኤድስ ስርጭት በህብረተሰቡ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ የበርካታ ፈጻሚ አካላትን የመፈጸም አቅም በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡ የመፈፀም አቅም ለመገንባት ከሚጠቀማቸው ስልቶች አንዱ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ሲሆን ይህንኑ ፋይናንስም ከተለያዩ አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች፣ ከአገር በቀል መያዶች እንዲሁም ከክልሉ መንግስት ያገኛል፡፡ይህን ከተለያዩ ምንጮ የተገኘ ሀብት ስራ ላይ ለማዋልም የሀብት ማስተላለፍ ስርዓት ተቀርፆ ለፈጻሚ አካላት እንዲሰራጭ/እንዲተላለፍ/ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ሆኖም ግን የሀብት ማሰባሰቡ ስራ ብዙም ትኩረት ያልተሰጠውና ለጋሽ ድርጅቶች በሚልኩት ገንዘብ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ ኤችአይቪኤድስ በክልሉ እያደረሰ ያለውን ጉዳትና ተጽዕኖ ከመቀነስ አንጻር ተመጣጣኝ ሀብት ማሰባሰብ አልተቻለም፡፡ የተሰባሰበውም ሀብት ቢሆን ፍትሃዊና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ስራ ላይ የማዋል ውሱንነት ይታያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተሰራጨው ሀብት በአግባቡ ስራ ላይ ውሎ በወቅቱ ሪፖርት የማይደረግበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በነዚህ ችግሮች ምክንያትም የደንበኞችን ፍላጎት ለማርካት አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በመቅረፍ የደንበኞችን ፍላጎት ለማርካት የሚያስችል አዲስ የስራ ሂደት መቅረጽ አስፈልጓል፡፡ ይህን አዲስ የስራ ሂደት ለመቅረጽም ነባሩን የስራ ሂደት ሁኔታ መቃኘት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በዚሁ መሰረት የፕሮጀክት ዝግጅትና ፋይናንስ አስተዳደር ነባሩ የስራ ሂደት ቅኝት ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

1. **የጥናቱ ዓላማ**

   አሁን ያለው የፕሮጀክት ዝግጅትና ፋይናንስ አሰተዳደር የስራ ሂደት ከመጠን፣ ከጥራጥ ከጊዜና ከወጪ አንፃር ለደንበኞች እየሰጠ ያለውን የአፈፃፀም ደረጃ ለመቃኘት ነው፡፡

## 2. የጥናቱ ግብ

ነባሩ የፕሮጀክት አዘገጃጀትና የፋይናንስ አስተዳደር የስራ ሂደት አሁን ያለበትን ደረጃ በመቃኘት በመጠን፣ በጥራት፣በጊዜና በወጪ ደንበኞችን የሚያረካ አዲስ የስራ ሂደት መዘርጋት ነው፡፡

## 3. የጥናቱ አስፈላጊነት

አዲሱ የፕሮጀክት አዘገጃጀትና ፋይናንስ አሰተዳደር የስራ ሂደት የደንበኞችን ፍላጎት በሚያረካ መልኩ ለመቅረጽ የሚያስችል የመነሻ ሀሳብ ለማግኘት ነው፡፡

## 4. የጥናቱ ወሰን /Scope/

4.1. ጥናቱ ከክልል እስከ ወረዳ የሚገኙ የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱን ማስተባበርያ ጽ/ቤቶች ነባሩን የፕሮጀክት ዝግጅትና ፋይናንስ አስተዳደር አሰራር ይቃኛል፡፡

4.2. ነባሩ የስራ ሂደት ቅኝት የሚያተኩረው ለመነሻነት በሚያገለግሉ ዋናዋና ጉዳዮች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

## 5. የጥናቱ ዘዴ

5.1. ከደንበኞች መካከል በናሙና የተመረጡ መ/ቤቶች መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ

5.2. የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ ሰራተኞችን ማነጋገር

5.3. የሴክሬታሪያት ጽ/ቤቱ የውስጥ መመሪያዎችና ደንቦችን መዳሰስ

5.4. ለመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት አጋዥ የሆኑ ዋቢ መጻህፍትን መቃኘትና የአሰራር መርሆዎችን መውሰድ

5.5. በፕሮጀክት ዝግጅትና ፋይናንስ አስተዳደር ዙሪያ የነበሩ አሰራሮችና ሰነዶችን መቃኘት

5.6. ለመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ከተመደቡ አማካሪዎች /ቄሳሮች/ ጋር መወያየት

## 6. ነባሩን የስራ ሂደት መተንተን

### 6.1. ነባሩ የስራ ሂደት የት ጀምሮ የት ያበቃል?

- የስራ ሂደቱ የሚጀምረው ለጋሽ ድርጅቶች ሊደግፉን ያሰቡትን የሀብት መጠን ሲያሳውቁን ነው፡፡
- የስራ ሂደቱ የሚያበቃው የተሰባሰበው ሀብት ለሚመለከታቸው ፈፃሚ አካላት ተላልፎና ስራ ላይ ውሎ የአፈፃፀም ሪፖርት ለለጋሽ ድርጅቶች ሲቀርብ ነው፡፡

## 6.2. <u>የስራ ሂደቱ ግብዓትና ውጤት</u>

### 6.2.1. <u>ግብዓት (In put)</u>

- ኤች አይ ቪ/ኤድስ ለመከ/መቆጣጠር የሚያስችል በቂ ፈንድ ያለማግኘት ችግር፣
- ደንበኞች ለሚጠይቁት የገንዘብ ድጋፍ ወቅታዊ ምላሽ ያለማግኘት ችግር
- ግልፅና ወጥነት ያለው የፋይናንስ አፈፃፀም መመርያ ያለማግኘት ችግር
- ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት ያለማግኘት ችግር፣

### 6.2.2. <u>ውጤት (Out Put)</u>

- ኤችአይቪ ኤድስን ለመከ/መቆ የሚያስችል የተገኘ፣ የተሰራጨና ስራ ላይ የዋለ ፈንድ፣
- ደንበኞች ለሚያቀርቡት የፈንድ ድጋፍ  የተሰጠ ወቅታዊ ምላሽ
- ለደንበኞች ግልፅ ሆኖ የተዘጋጀ የፋይናንስ አፈፃፀም መመርያ
- በወቅቱና ጥራቱን ጠብቆ የቀረበ ሪፖርት፣

### 6.2.3. <u>የግብ ስኬት</u>(Out Come)

ከተለያዩ ምንጮች በተገኘ በቂና በአግባቡ ስራ ላይ በዋለ ፈንድ በተገነባ የመፈፀም አቅም

ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከ/መቆ የተሰጠ ዘርፈ ብዙ ምላሽ

## 7. የነባሩ የስራ ሂደት ፍሰት (High Level Map)



# 8. የነባሩ የስራ ሂደት ዝርዝር ፍሰት (Detail Map)




2
2
2
2
ዩንዳፍ ገንዘቡን ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ያስተላልፋል
የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ገንዘቡን ለክልል ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ሴክ/ጽ/ቤትና ለወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ያስተላልፋል
የክልሉ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ሴክ/ጽ/ቤት ገንዘቡን ለዞን ኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከ/መቆ ማስ/ጽ/ቤቶች ያስተላልፋል
የዞን ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ማስ/ጽ/ቤት ገንዘቡን ለፈጻሚ አካላት ያስተላቂፋሉ
ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ መዝገብ ቤት ይገባል
ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ለኃላፊው ይቀርባል
ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ለዕቅድና ፕ/አፕሬዛል ይመራል
በዕቅድና ፕ/አፕሬዛል ቅድመ ግምገማ ይደረጋል
የቅድመ ግምገማው ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ቀርቦ ይፀድቃል
የለም
አዎ
3
3
3
3


3
3
3
3
ለሪቪው ቦርድ ቀርቦ ምዘና ይካሄድበታል
የሪቪው ቦርድ
የውሳኔሃሳብ
በጽ/ቤት ኃላፊው
ይፀድቃል
የለም
ከፈፃሚው አንል ጋር የፋይናንስ ውል ስምምነት ይያዛል
የፋይናንስ ውል
ስምምነቱ በኃላፊው
ይፀድቃል
የለም
አዎ
4
4
4


4
4
4
የፀደቀው የፋይናንስ ውል ስምምነት ለክልል ፋይናንስ ክፍል ይመራል
የክልል ፋይናንስ ክፍል
ገንዘብ እንዲያስተላልፍ በደብዳቤ ይታዘዛል
የክልል ፋይናንስ ክፍል
ለፈፃሚ አካላት፣ ለሴክተሮችና ለዞን ማስተባበርያ ጽ/ቤቶች ገንዘብ ያስተላልፋል
የዞን ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ማስ/ጽ/ቤት ማስ/ጽ/ቤቶች በስራቸው ለሚገኙ ወረዳዎች ገንዘብ ያስተላልፋሉ
ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ይቀርባል
ለዞን የመንግስት ሴክተሮች የተመደበላቸው በጀት በደብዳቤ ይገለፅላዋል
ለወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶች የተመደበላቸው የበጀት ድልድል በደብዳቤ ይገለፅላቸዋል
5
5
5
5


5
5
5
5
ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ መዝገብ ቤት ይገባል
ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ለኃላፊው ይቀርባል
ለሪቪው ቦርድ/ ለስራ አመራር ኮሚቴ/ ቀርቦ ምዘና ይካሄድበታል
የሪቪው ቦርድ የውሳኔ ሀሳብ ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ቀርቦ ይፀድቃል
የለም
አዎ
ከፈፃሚው አካል ጋር የፋይናንስ ውል ስምምነት ይያዛል
6
6
6


6
6
6
የፋይናንስ ውል ስምምነቱ ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ቀርቦ ይፀድቃል
የለም
አዎ
የፀደቀው የፋይናንስ ውል ስምምነት ለፈፃሚው አካልና ለዞን ፋይናንስ ክፍል ይመራል
የዞን ፋይናንስ ክፍል ገንዘቡን ለፈፃሚው አካልና ለወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶች እንዲያስተላልፍ በደብዳቤ ይታዘዛል
የዞን ፋይናንስ ክፍል ገንዘቡን ለፈፃሚው አካልና ለወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶች ያስተላልፋል
7
7


7
7
የወረዳ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ማስ/ጽ/ቤቶች ለወረዳ የመንግስት ሴክተሮችና ሌሎች ፈፃሚ አካላት የገንዘብ ድልድል ያደርጋሉ
ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ይቀርባል
ለወረዳ የመንግስት ሴክተር ጽ/ቤቶች የተመደበላቸው ገንዘብ በደብዳቤ ይገለፅላቸዋል
ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ መዝገብ ቤት ይገባል
ፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ለኃላፊው ይቀርባል
ለሪቪው /ስራ አመራር/ ቦርድ ቀርቦ ምዘና ይካሄድበታል
የሪቪው ቦርድ የውሳኔ ሀሳብ ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ቀርቦ ይፀድቃል
የለም
አዎ
8
8
8


8
8
8
ከፈፃሚ አካላትና ከወረዳ ሴክተር ጽ/ቤቶች ጋር የፋይናንስ ውል ስምምነት ይያዛል
የፋይናንስ ውል
ስምምነቱ ለጽ/ቤቱ
ኃላፊ ቀርቦ ይፀድቃል
የለም
አዎ
የፀደቀው የፋይናንስ ውል ስምምነት
ለፈፃሚው አከልና ለወረዳ ፋይናንስ ክፍል
ይመራል
የወረዳ ፋይናንስ ክፍል ገንዘቡን ለፈፃሚው አካልና ለወረዳ የመንግስት ሴክተር ጽ/ቤቶች
እንዲያስተላልፍ በደብዳቤ ይታዘዛል
የወረዳ ፋይናንስ ክፍል ገንዘቡን ለፈፃሚው አካልና ለወረዳ የመንግስት ሴክተር ጽ/ቤቶች
ያስተላልፋል
9
9


9
9
በየደረጃው የሚገኙ ፈፃሚ አካላት የተላከላቸውን ገንዘብ በአግባቡ ስራ ላይ ስለማዋላቸው እና በወቅቱም እንዲያወራርዱ ክትትል ይደረጋል
በፈፃሚ አካላት የቀረበ ሂሳብ ይወራረዳል
የተወራረደው ሂሳብ ኮድ ይደረጋል
ኮድ የተደረገው ሂሳብ በፒች ትሪ አካውንቲንግ ፕሮግራም በኮምፒተር ይመዘገባ
በኮምፒተር የተመዘገበው የፋይናንስ መረጃ ትክክል ስለመሆኑ ፕሪንት ተደርጎ ከኦሪጅናል ሰነዶች ጋር ይናበባል
የ SOE report በማዘጋጀት ሂሳብ ለለጋሽ ድርጅቶች ይወራረዳል
ዓመታዊ ሂሳብ በመዝጋት የተለያዩ የፋይናንስ ሪፖርቶች ይዘጋጃሉ
10

10

የተዘጋጁት የፋይናንስ ሪፖርቶች ለፌደራል ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከ/መቆ ሴክ/ጽ/ቤትና ለሚመለከታቸው አካላት ይላካሉ

↓

ለፌደራል ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከ/መቆ ሴክ/ጽ/ቤት በተላከው ሪፖርት መነሻነት ሂሳብ በውጭ ኦዲተሮች ይመረመራል

↓

በውጭ ኦዲተሮች በሚቀርበው ረቂቅ አስተያየት መሰረት ምላሽ ይሰጣል

↓

በውጭ ኦዲተሮች በሚቀርበው የማጠቃለያ ሪፖርት አስተያየት መሰረት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል

↓

ከተለያዩ ምንጮች በተገኘ በቂና በአግባቡ ስራ ላይ በዋለ ፈንድ በተገነባ የመፈፀም አቅም ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከ/መቆ የተሰጠ ዘርፈ ብዙ ምላሽ

## 9. ነባሩን የስራ ሂደት መረዳት

### 9.1. የስራ ሂደቱ ምን ውጤት ያስገኛል?

በፈንድ የተገነባ የመፈፀም አቅምና በወቅቱ የተዘጋጀ የፋይናንስ የአፈፃፀም ሪፖርት

### 9.2. የስራ ሂደቱ ይህን ውጤት ለምን አስገኘ?

ኤችአይቪ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በፈንድ የተገነባ የመፈፀም አቅም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

### 9.3. የስራ ሂደቱ ደንበኞችና ፍላጎት

<table>
<tr><th>ተ.ቁ /No./</th><th>ደንበኞች /Customers/</th><th>የደንበኞች ፍላጐት /Customers need/</th></tr>
<tr><td>1</td><td>የመንግስት መ/ቤቶች<br>- ሴክተር መ/ቤቶች<br>- ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት<br>- የልማት ፕሮጀክቶችና ፋብሪካዎች</td><td rowspan="7">▪ ኤችአይቪ ኤድስን ለመከ/መቆ የሚያስችል በቂ ፈንድ በወቅቱ የማግኘት ፍላጎት፣<br>▪ በፈንድ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙርያ ድጋፍ የማግኘት ፍላጎት፣<br>▪ አዘጋጅተው ያቀረቡት የወጪ መግለጫ ሪፖርት (SOE Report) በወቅቱ እንዲወራረድላቸው የመፈለግ፣</td></tr>
<tr><td>2</td><td>ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖች ማህበራት</td></tr>
<tr><td>3</td><td>አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች</td></tr>
<tr><td>4</td><td>የሲቪክ ማህበራት</td></tr>
<tr><td>5</td><td>አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች</td></tr>
<tr><td>6</td><td>የእምነት ተቋማት</td></tr>
<tr><td>7</td><td>የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች</td></tr>
<tr><td>8</td><td>ፌደራል ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤትና ሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች</td><td>▪ ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት የማግኘት ፍላጎት፣<br>▪ ለስራ ምቹ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር መፈለግ፣<br>▪ ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት የማግኘት ፍላጎት፣<br>▪ የሚለግሱት ሀብት ለተፈለገው ዓላማ እንዲውል መፈለግ፣</td></tr>
<tr><td>9.</td><td>ህብረተሰቡ</td><td>▪ ሀብት እንዲሰባሰብና በተገቢው መንገድ ስራ ላይ እንዲውል የመፈለግ፣<br>▪ ስለተሰባሰበውና ስራ ላይ ስለዋለው ገንዘብ ወቅታዊ መረጃ የማግኘት ፍላጎት፣</td></tr>
</table>

## 9.4. ሌሎች ባለድርሻዎችና ፍላጎቶቻቸው

| ተ.ቁ /No./ | ባለድርሻዎች /Stakeholder/ | ኃላፊነታቸው /ድርሻቸው/ | የባለድርሻዎች ፍላጐት / Stakeholders' need/ |
|---|---|---|---|
| 1 | በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት ምክር ቤቶች | - ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመከ/መቆ አገልግሎት የሚውል ዓመታዊ መደበኛ በጀት መመደብ | - በቂ ፈንድ እንዲሰባሰብና በወቅቱና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል፣<br>- ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት ማግኘት፣ |
| 2 | በየደረጃው የሚገኙ የኤችአይቪ ኤድስ መከ/መቆ ምክር ቤቶች | - ኤች.አይ.ቪ.ኤድስን መከ/መቆ የሚያስችል እርዳታና ድጋፍ እንዲሰበሰብና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል አመራር መስጠትና አፈፃፀሙንም መከታተል፣<br>- የፋይናንስ ዕቅድና የአጠቃቀም ሪፖርት ማዳመጥ፣ መገምገምና ማፅደቅ | - በቂ ሀብት እንዲሰባሰብና በወቅቱ ስራ ላይ እንዲውል<br>- ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ ዓመታዊ ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት የማግኘት ፍላጎት፣ |
| 3 | በየደረጃው የሚገኙ የኤችአይቪ ኤድስ መከ/መቆ ሥራ አመራር ቦርድ/ኮሚቴ | - በሴክ/ጽ/ቤቱ ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ዓታዊ የስራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ ገምግሞ ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ ያስፀድቃል<br>- በበጀት ውስጥ ያልተመለከተ ገቢ ሲገኝ በስራ ላይ በማዋል ጠ/ጉባኤው ሲሰበሰብ በጀቱን ያስፀድቃል፣ ለሴክሬታሪያቱ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶችን ይገመግማል ያፀድቃል፣ | - ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም ሪፖርት የማግኘት ፍላጎት፣<br>- ፍትሃዊ ለሆነ የሀብት አጠቃቀም የተዋቀረው አደረጃጀት በአግባቡ እየሰራ መሆኑን የማወቅ ፍላጎት |
| 4 | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ | - ዓመታዊ መደበኛ በጀትን በወቅቱ ማስተላለፍ፣<br>- ከተባበሩት መንግስታት ድርጅቶች (UNDAF) የሚላከውን በጀት የማስተላለፍ | ዕቅድና ሪፖርት በወቅቱ ማግኘት |

## 9.5. የነባሩ የስራ ሂደት የአፈፃፀም ደረጃ

| ተ.ቁ | ዋና ዋና ተግባራት | ደረጃ (Step) | ጊዜ (Time) (በቀን) | ወጪ (Cost) (በብር) | ጥራት (Quality) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **ፈንድ ማፈላለግ/ማሰባሰብ/** | | | | |
| 1.1. | በግሎባል ፈንድ/ኢምሳፕ/ | 5 | 3.25 | 686.09 | |
| 1.2. | ዩንዳፍ | 12 | 7.75 | 1,636.06 | |
| 2 | **ፈንድ ማሰራጨት** | | | | 67.67% = መካከለኛ |
| 2.1. | በግሎባል ፈንድ/ኢምሳፕ/ | 39 | 10,737.00 | 2,269,929.12 | |
| 2.2. | ዩንዳፍ | 2 | 2 | 422.21 | |
| 3. | ሂሳብ ማወራረድና የሀብት አጠቃቀም ሪፖርት ማቅረብ | 8 | 16,882 | 5,313,246.34 | 62.67% = መካከለኛ |
| 4. | ሂሳብን በውጭ ኦዲተሮች ማስመርመር | 3 | 40 | 8,444.18 | 48% = ዝቅተኛ |
| | የጽህፈት መሳርያዎች | | | 8,780.00 | |
| | **ድምር** | 69 | 27,672 | 7,603,144.00 | |
| | | | | | |

**ማሳሰቢያ**

- ጥራት የተመዘነው ከደንበኞች በተሰባሰበ መረጃና በተሰጠ አስተያየት ነው
- ወጪውን በተመለከተ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ያለውን ያካተተ ሲሆን በዚህም መሰረት ለደመወዝ ብር. 5,841,684.00፣ ለክትትል ብር. 1,749,380.00፣ ለረቪው ቦርድ አበል 3,300.00 እና ለጽህፈት መሳርያ ብር. 8,780.00 ነው።

## 9.6. የስራ ሂደቱ ችግሮች፣ ህጎችና ታሳቢዎች (Problems, Rules & Assumptions)

| *ተ.ቁ (No)* | *ችግር (Problem)* | *የችግሩ ምንጭ (Rules)* | *ታሳቢዎች (Assumptions)* | *ታሳቢዎችን መሻር (Untrue assumptions)* |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የደንበኞችን ፍላጎት ሊያረካ የሚችል በቂ ፈንድ ባለመገኘቱና ባለመሰራጨቱ ደንበኞች ኤች.አይ.ቪ.ኤድስን ለመከ/መቆ የሚያከናውኑት ተግባር አነስተኛ መሆኑ | ▪ በልማድ እየተሰራበት ያለው ፈንድ የማሰባሰብ ተግባር ከፌደራል ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት፣ ከክልሉ መንግስትና ከዩንዳፍ ብቻ በመጠበቅ ላይ የተመሰረተ መሆኑ<br>▪ በቂ ፈንድ ለማሰባሰብ የሚያስችል የአራር ስርዓት አለመኖር | ▪ ከፌደራል ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤት፣ከክልሉ መንግስትና ከዩንዳፍ የሚመጣው ፈንድ በቂ ነው ብሎ ማሰብ<br>▪ ባለው የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ፈንድ ማግኘት ይቻላል ብሎ ማሰብ | ▪ ከእነዚህ አካላት የሚገኘው ፈንድ የደንበኞችን ፍላጎት ለማረካት በቂ አልሆነም<br>▪ ባለው የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት በቂ ፈንድ ማሰባሰብ አልተቻለም |
| 2. | ለፈፃሚ አካላት የሚላከው ገንዘብ ወቅታዊ ባለመሆኑ የአፈፃፀም መዘግየትንና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት መቀነስን ማስከተሉ | - በፕሮጀክት ፕሮፖዛል የሚቀርቡ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄዎች በክልል በዞንና በወረዳ በሪቪው ቦርድ የሚታዩበት ስርዓት መኖሩ<br>- የተራዘመ/የተንዛዛ/ የፈንድ አስተላለፍ ስርዓት( ከክልል ለዞን ከዞን ለወረዳ ማስ/ጽ/ቤት ከወረዳ ለፈፃሚ አካላት) መኖር (በሴክ/ጽ/ቤት ማኔጅሜንት ኮሚቴ በተወሰነው መሰረት) | - የፕሮጀክት ምዘናው በሪቪው ቦርድ ቢገመገም ግልፅና ውጤታማ የሆነ የፈንድ ስርጭት ይኖራል የሚል ታሳቢ<br>- ለየወረዳ ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከ/መቆ ጽ/ቤቶችና ፈፃሚ አካላት ፍትሃዊ የሆነ የፈንድ ድልድል ለማድረግ ድልድሉ ከክልል ሴክ/ጽ/ቤት ይልቅ በዞን ማስ/ጽ/ቤት በኩል ቢደረግ ይሻላል የሚል ታሳቢ መኖር | - ፕሮጀክቶችን በሪቪው ቦርድ ማስገምገሙ የሚጠበቀውን ያህል ግልፅና ውጤታማ የሆነ የፈንድ ስርጭት አላመጣም<br>- የዞን ማስ/ጽ/ቤቶች በስራቸው ለሚገኙ ወረዳዎች የፈንድ ድልድል አለማድረጋቸው ድጋፋዊ ክትትል ከማድረግ አያግዳቸውም |

| ተ.ቁ (No) | ችግር (Problem) | የችግሩ ምንጭ (Rules) | ታሳቢዎች (Assumptions) | ታሳቢዎችን መሻር (Untrue assumptions) |
|---|---|---|---|---|
| 3 | ሂሳብ ወቅቱን ጠብቆ ባለመወራረዱ በለጋሽ ድርጅቶች አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማስከተሉ | - በፈንድ አጠቃቀም ዙርያ ለዞንና ወረዳ ማስ/ጽ/ቤቶች ሙሉ ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር አለመሰጠቱ(በበጀት ዝውውር ዙርያ )<br>- ፈፃሚ አካላት ሂሳባቸውን በወቅቱ እንዲያወራርዱ የሚያስችል የተጠናከረ የክትትል ስርዓት አለመኖር | - በዞንና በወረዳ ደረጃ ያሉ ባለሙያዎች የአቅም ውሱንነት ስላለባቸው የሚላክላቸውን ፈንድ በአግባቡ ስራ ላይ ሳያውሉት ይችላሉ የሚል ታሳቢ መኖር<br>- ፈፃሚ አካላት የፋይናንስ ውል እስከያዙ ድረስ በራሳቸው ተነሳሽነት ሂሳባቸውን ያወራርዳሉ የሚል ታሳቢ መኖር፣ | - አቅማቸው ከተገነባና ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር ከተሰጣቸው የተላከላቸውን ፈንድ በአግባቡ ስራ ላይ ያውሉታል<br>- ፈፃሚ አካላት በራሳቸው ተነሳሽነት ሂሳባቸውን በወቅቱ ሊያወራርዱ አልቻሉም፤ |
| 4 | በፈፃሚ አካላት የሚወራረድ ሂሳብና የሚቀርብ የፋይናንስ ሪፖርት ጥራቱን የጠበቀ ባለመሆኑ በለጋሽ ድርጅቶችና በሌሎች ሪፖርት ፈላጊ አካላት የአፈፃፀም ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማስከተሉ | ▪ ወጥና የተሟላ የፋይናንስ አፈፃፀም መመርያ ባለመኖሩና ለፈጻሚ አካላትም ተገቢው ኦረንቴሽን ባለመሰጠቱ<br>▪ በክልሉ ከተለያዩ ፈፃሚ አካልት ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመከ/መቆ ስራ ላይ እየዋለ ያለውን ሀብት ለማወቅ የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩ | - የተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች የተለያየ የፋይናንስ አፈፃፀም መመርያ ስላላቸውና ከእነሱ ፍላጎት አንፃር አንድ ወጥ መመርያ ማዘጋጀት አይቻልም የሚል ታሳቢ መኖር<br>- አስቀድሞም ገንዘቡ ሲለቀቅ ፈጻሚ አካላት በሂሳብ አያያዝ ዙርያ ተገቢው ዕውቀት ስላላቸው ኦረንቴሽን ባይሰጣቸውም ሂሳብ በጥራት ይሰራሉ የሚል ታሳቢ መኖር | - የሁሉንም ፈፃሚ አካላት ፍላጎት ያካተተ ወጥ የሆነ የፋይናንስ አፈፃፀም መመርያ ማዘጋጀት ይቻላል<br>- ፈፃሚ አካላት በሴክ/ጽ/ቤታችን የፋይናንስ አፈፃፀም ዙርያ የተሟላ ግንዛቤው የላቸውም |

| ተ.ቁ (No) | ችግር (Problem) | የችግሩ ምንጭ (Rules) | ታሳቢዎች (Assumptions) | ታሳቢዎችን መሻር (Untrue assumptions) |
|---|---|---|---|---|
| 5 | በክልሉ በተለያዩ አካላት ኤች.አይ.ቪ.ኤድስን ለመከ/ መቆ ተግባራት ስራ ላይ እየዋለ ያለውን የፈንድ መጠን በሙሉ ለማወቅ ባለመቻሉ ፍትሀዊ የሆነ የፈንድ ስርጭት ለማድረግ አለመቻሉ | ሴክ/ጽ/ቤቱ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በመከ/መቆ ተግባራት የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ አካላት በቅርበት መከታተል እንደሚችል በሴክሬታሪያቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 73/94 አንቀጽ 15(3) የተደነገገ ቢሆንም እነዚሁ አካላት ስራ ላይ የሚያውሉትን የፈንድ መጠንም ማሳወቅ እንዳለባቸው የሚያመላክት አስገዳጅነት ያለው የአፈፃፀም ደንብ አለመኖሩ | ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በመከ/መቆ ተግባራት ዙርያ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ አካላት ከራሳቸው በጀት ስራ ላይ የሚያውሉትን የፈንድ መጠን አዋጁን መነሻ በማድግ በተጠየቁ ጊዜ ያሳውቃሉ የሚል ታሳቢ መኖር | አሁን ባለው አዋጅ መነሻነት በሚደረግ ክትትልና በተጠየቁት መሰረት ስራ ላይ የሚያውሉትን የፈንድ መጠን ሊያሳውቁ አልቻሉም |
| 6 | ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመከ/መቆ ተግባራት ከተለያዩ ምንጮች የሚሰባሰበው ገንዘብ በአግባቡ ስራ ላይ እየዋለ አይደለም የሚል የደንበኞች ቅሬታ መኖርና ለዚሁ ቅሬታም ተገቢ ምላሽ ባለመሰጠቱ በሽታውን በመከ/መቆ ረገድ የህብረተሰቡ ተሳትፎ መቀነስ | - ከተለያዩ ምንጮች የተሰባሰበው ገንዘብ በአግባቡ ስራ ላይ የዋለ ስለመሆኑ የሚወራረደውም በወጪ ሂሳብ ማወራረጃ ሪፖርት (SOE report) በመሆኑና ይኸው የማወራረጃ ስርዓት ፈንዱ በአግባቡ ስራ ላይ የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ የማያስችል መሆኑ | - በሚቀርብ የወጪ ሂሳብ ማወራረጃ ሪፖርት (SOE report ) ብቻ ትክክለኛ ስራ መከናወኑን ማወቅ ይቻላል የሚል ታሳቢ መኖር | በ SOE report ብቻ በሚወራረድ ሂሳብ ገንዘቡ በአግባቡ ስራ ላይ የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም |